# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

# Monthly Met. News



የወቅታዊ ትንበያ የምክክር መድረኩ ሲካሄድ




የአየር ሁኔታ ሞዴል አጠቃቀም ሥልጠና ተሳታፊዎች

## ቅጽ 4 ቁጥር 3 የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

መስከረም 2010 ዓ.ም

# ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ያለፈውን የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና በመጪው በጋ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያ ደንበኞቹ እና ባለድርሻዎቹ በተገኙበት ይፋ አደረገ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ያለፈውን የክረምት ወቅት የአየር ጠባይ ግምገማና በመጪው በጋ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ትንበያ ደንበኞቹና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ይፋ ያደረገው መስከረም 25 ቀን 2010 ዓ.ም በኢንተርኮንትኔንታል ሆቴል የምክክር መድረክ ላይ ነው፡፡

የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ሲሆኑ የአየር ጠባይ ተጽዕኖ ሁሉንም ማኅበረሰብ፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማትንና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚያካትትና የሚመለከት ጉዳይ ነው። ኤጀንሲውም ይህንን ኃላፊነት በዋናነት ወስዶ የሚሠራ ቢሆንም የባለ ድርሻና ተባባሪ አካላት እንዲሁም የደንበኞች ሚና እጅግ ወሳኝነት አለው። በመሆኑም፣ ዘርፉ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲደርስ መረጃዎቹን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከሚጠቀሙ ባለ ድርሻ አካላትና ተገልገጋዮች ጋር የጋራ መድረክ መፍጠርና ውይይት በማድረግ አብሮ በማቀድና አፈጻጸምን መገምገም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የውይይት መድረክ እንዲዘጋጅ ተደርጓል ብለዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘውም አሁን በዓለማችን የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎች ለተለያዩ ሴክተሮች በተለይም በግብርና፣ በውኃ ልማት፣ በጤና፣ በአቪዬሽን፣ በቱሪዝም ኢንዱስትሪ፣ በትራንስፖርት፣ በግንባታና በመሳሰሉት ዘርፎች አስፈላጊነታቸው እየጨመረ የመጣበት ጊዜ መሆኑን እያየን በመጣንበት ወቅት፣ ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ አገልግሎቱን ከጊዜ ወደ ጊዜ በከፍተኛ ሁኔታ እያሻሻለ የመጣ ቢሆንም አሁንም ከተጠቃሚው ፍላጎት አንጻር ብዙ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን የሚካሄደው ፈጣንና ዘላቂ ልማት በሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ከተደገፈ ውጤቱ ያማረ ሊሆን እንደሚችል እየታወቀ መጥቷል›› ብለዋል፡፡

አቶ ፈጠነ ንግግራቸውን በመቀጠልም፣ ‹‹ኤጀንሲው ከአየር ሁኔታና ጠባይ ጋር ግንኙነት ባላቸው የተፈጥሮ አደጋዎች ላይ ቅድመ-ዝግጅትን በማጠናከርና የአገሪቱን ዕድገት ዘላቂነት ለማረጋጥ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በመሰብሰብ፣ ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎችን በመከታተል እንዲሁም ሳይንሳዊ ልኬቶቹንና የትንበያ ሞዴሎችን በመተንተንና በመገምገም ለተለያዩ የሶሽዮ-ኢኮኖሚክ ሴክተሮች የአጭር፣ የመካከለኛና

የረጅም ጊዜ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያና ቅድመ-ማስጠንቀቂያ አገልግሎቶችን በወቅቱ በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ ይህ የዛሬው መድረክም ኤጀንሲው ባለፈው ክረምት ወቅት የሰጠው ትንበያ በተጨባጭ ከተከሰተው ጋር በማነጻጸር የምንገመግምበት፣ የአገልግሎት አሰጣጡ ምን እንደሚመስል የሚታይበት እንደመሆኑ መጠን በዓመት ሦስት ጊዜ ለአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችና ባለ-ድርሻ አካላት የሚያቀርበው ያለፈው ወቅት ትንበያ ግምገማና የመጪው በጋ ወቅት ትንበያ ከኤጀንሲው አገልግሎት አሰጣጥ ጋር ተቀናጅቶ እንዲገመገም መደረጉ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡ ስለሆነም የሚቲዎሮሎጂ ዘርፉ የሚጎለብትበትን እንዲሁም እናንተ ከዘርፉ የምትጠብቁትን የአገልግሎት ጥራት መሻሻል በሚገባቸው ደረጃ እንዲሻሻሉ ሰፊ ውይይትና ምክክር ማድረግ ይጠበቃል፡፡ ኤጀንሲው በየጊዜው በሀገራችን የተለያ ቦታዎች ሊፈጠሩ የሚችሉትን የአየር ሁኔታ ገጽታዎችን አስቀድሞ በመተንበይ የቅድመ-ማስጠንቀቂያና መግለጫዎችን በቅርበት ክትትል እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

በዚሁ የአንድ ቀን የምክክር መድረክ ላይ ከኤጀንሲው የወጣው መግለጫ እንደሚያመለክተው ባለፈው ክረምት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደተስተዋለባቸውና በተለይም በዘንድሮ ክረምን በነሐሴና መስከረም ወራት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ በተከታታይ ቀናት በመጣሉ ለወንዞች ሙላትና ለቅጽበታዊ ጎርፍ መከሰት አስተዋጽዖ ያደረገ ከመሆኑም በላይ ነጎድጓዳማና በረዶ አዘል ከባድ ዝናብ በንብረትና በሰው ሕይወት ላይ አደጋ እንዳስከተለ መረጃዎችን በማጣቀስ በባለሙያዎች ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም ባለፈው ክረምት ወቅት በመላው ሀገሪቱ ላይ የነበረው የተለያየ መጠን ያለው የዝናብ መጠንና ስርጭት በአብዛኛው የተስተካከለ በመሆኑ በዚህ ወቅት ለተካሄዱት የግብርና ሥራና የውኃ አቅርቦት ምቹ ሁኔታን የፈጠረ መሆኑ ተገልጿል፡፡

በአጠቃላይ የዘንድሮ ክረምት ወቅት ዝናቡ መደበኛውን ፈር ተከትሎ የጀመረ ቢሆንም ከሰሜን ምስራቅና ከምስራቅ ኢትዮጵያ የመውጫው ጊዜ ላይ ግን በመጠኑ መዘግየት እንደተስተዋለ ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኤጀንሲው ለመጪው በጋ ወቅት ትንበያ የሰጠ ሲሆን በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቃማ የአየር ጠባይ እንደሚያመዝንና በትንበያው መሠረት ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው የሆኑት የደቡብና የደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች

መደበኛና በአንዳንድ ስፍራዎቻቸው ላይ ከመደበኛው በታች ዝናብ ሊኖራቸው እንደሚችል ተጠቁሟል፡፡

በበጋው ወቅት በመደበኛው ሁኔታ የሚዘወተረው የውርጭ ክስተትና የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜን በተመለከተ የኤጀንሲው ትንበያ እንደሚያሳየው በመጪው በጋ ወቅት የእነዚህ ክስተቶ ጥንካሬ አልፎ አልፎ ሊጨምር እንደሚችል ተብራርቷል፡፡ ስለሆነም ኅብረተሰቡ በመጪው በጋ ወቅት የሚጠበቀውን የአየር ጠባይ ክስተተን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚህ ወቅት የሚከናወነውን የግብርና ሥራና ሌሎች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሥራዎችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካር አጠናክሮ እንዲቀጥል ኤጀንሲው ማሳሰቢያ ሰጥቷል፡፡ በተለይም ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት በደቡብና ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ የዝናብ መጠንና ስርጭት እጥረት ሊያጋጥም ስለሚችል አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ በሚቀጥለው የበጋ ወቅት የሚገኘውን ርጥበት በአግባቡ እንዲጠቀምበት ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ባዘጋጀው በዚህ የምክክር መድረክ ላይ ከአስራ አንዱም የኤጀንሲው የክልል ሚቲዎሮሎጂ ማዕከላት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የተገኙ ሲሆን ሁሉም ትንበያውን በማውረድ በየአካባቢያቸው የሚኖረውን የአየር ጠባይ ትንበያ እንዲያቀርቡ አቅጣጫ ተቀምጧል፡፡ በዕለቱም ከፌዴራል መንግስታዊ ተቋማት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የተጋበዙ እንግዶች በምክክር መድረኩ ላይ መገኘታቸው ታውቋል፡፡ በምክክር መድረኩ ላይም 13 /አስራ ሦስት/ የጥናት ጽሑፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡





# የአየር ሁኔታንና የአየር ንብረት ሞዴልን ወደ ስራ ለማስገባት ስልጠና ተሰጠ

ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ እ.አ.አ. መጋቢት 2017 2017 በUNDP ፕሮጀክት የገዛውን ከፍተኛ ስራ የመፈፀም ብቃት ያለው ኮምፒውተር /High performing Computer (HPC) / የገዛ ሲሆን ይህንን መሳሪያ ስራ ላይ ለማዋል ከተለያዩ የስራ ክፍሎች የተወጣጡ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎችና ሃላፊዎች ስልጠናውን ወስደዋል፡፡

ስልጠናው የተሰጠው ከነሃሴ 22 እስከ ጳጉሜ 3 2009 ዓ.ም ከበይነ መንግስታት የልማት ባለስልጣን የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ማዕከል በመጡት በዶ/ር ዘውዱ ተሰማ ሲሆን ስልጠናውም ቦሌ በሚገኘው የኤጀንሲው የማኔጅመትን መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ነው፡፡

ይህ መሳሪያ ስራ ላይ ሲውል የዓየር ሁኔታን ከአንድ ሰዓት ባለነሰ ጊዜ መስጠት የሚያስችልና አካባቢያዊ ትንበያዎችን እንዲሁም የአየር ጠባይን በተለያዩ ወቅቶች በተለያዩ የትንበያ ዘዴዎች /statically and dynamic/ በመጠቀም መተንተይ የሚያስችል ሲሆን ይህ መሳሪያ 26 ሞድ ያለው፣ ሃክ የማይደረግና በቀላሉ ለቫይረስ ተጋላጭ ያልሆነ መሳሪያ ነው፡፡

በተያያዘ ዜና ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከአሜሪካው የብሔራዊ ውቅያኖስና ከባቢ አየር ኤጀንሲ (National Oceanic and Atmospheric Agency, NOAA) እና ከUSAID ጋር በመተባበር በአየር ጠባይ ክትትልና ትንበያ (Climate Monitoring and Forecasting) ዙሪያ ከኤጀንሲው ዋና መስሪያቤትና ከክልል የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከላት ለተውጣጡ የሚቲዎሮሎጂ ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ስልጠናው የኤጀንሲውን ባሙያዎች ክህሎት በማሳደግ ከአለም የአየር ጠባይ ማዕከላት የሚወጡ ዳታዎችንና መረጃዎችን ለመተንተን የሚረዱ ሶፍትዌሮችን አጠቃቀም እንዲሁም በዳይናሚካል ሞዴሎችን በመጠቀም የወቅት ትንበያ ለመስጠት የሚያስችል ስልጠና ነበር፡፡ ስልጠናውን የNOAA ሳይንቲስቶቹ ዶ/ር ዋሲላ ቺአው እና ዶ/ር ቫድላማኒ ኩማር ለ7 ተከታታይ ቀናት የተሰጠ ሲሆን በስልጠናው ላይ 32 የኤጀንሲው ባለሙያዎች ተሳታፊ ሆነዋል፡፡



ሥልጠናው ሲካሄድ

## ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በBRACED (Building Resilience and Adaptation to Climate Extremes and Disasters) ፕሮጀክት ከለጋሽ ድርጅቶች በተገኘው ድጋፍ የተከላቸውን ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን እንደሚንከባከቡ የሀገር ሽማግሌዎች ቃል በመግባት ተረክበዋል፡፡

በፕሮጀክቱ 25 ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎች የተገዙ ሲሆን እነዚህም በሦስት ክልሎች ማለትም በአፋር፣ በሶማሌና በደቡብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቶች የተተከሉ መሆናቸው እና የሦስቱ ክልሎች ተወካዮች፣ የክልል አመራሮች፣ የጋሞጎፋ ዞን አመራሮችና በአርባ ምንጭ ዙሪያ የሚገኙ ወረዳ አመራሮች እንዲሁም ከኦርጎባ ቀበሌ የሀገር ሽማግሌዎችና የአከባቢው ነዋሪዎች በአጠቃላይ ከ300 በላይ ተሳታፊዎች በተገኙበት መስከረም 19 ቀን 2009 የምረቃ ስነስርዓት ተካሄዷል፡፡

የምረቃ ሥነ ሥርዓቱን በንግግር የከፈቱት የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር አቶ ፈጠነ ተሾመ ባስተላለፉት መልዕክት አገራችን የሚያስፈልጋት የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ ፍላጎት ከቆዳ ስፋትና መልከዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ጋር ተያይዞ ቁጥሩ ከፍተኛ መሆኑን ኤጀንሲው ቀደም ብሎ ባዘጋጀው ማስተር ፕላን ላይ ማመላከቱን ጠቅሰው ይሄውም ከፍተኛ ሀብትና አቅም የሚጠይቅ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህንን ለማሟላት ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶችና ተባባሪ አካላት ጋር ተቀራርበን በመሥራት የጣቢያዎቻችንን ቁጥር በተለይም የዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መሳሪያዎች ቁጥር ለማሳደግ ያስቀመጥነውን ዕቅድ ማሳካት መቻላችን እንደ ተቋም የምንከተለው ስትራቴጂ ውጤት እያፈራ መምጣቱን ያመላከተ ነው ብለዋል፡፡ ለዚህም አቶ ፈጠነ ለአብነት ያነሱት በBRACED ፕሮጀክት የተገዙ ሀያ አምስት (25) ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያዎችን በመጀመሪያው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንደ ሀገር ከነበረው 25 AWS ጋር ካነፃፀሩ በኋላ በዚህ ፕሮጀክት ብቻ ይህን ያክል መሣሪያ በድጋፍ እንድናገኝ ለረዱን ሁሉም የፕሮጀክቱ ለጋሽና ተባባሪ አካላት ትልቅ ምስጋና ይገባቸዋል በማለት የጋሞጎፋ ዞንም የዚህ ዕድል ተጠቃሚ በመሆናችሁ እንኳን ደስ አላችሁ ለማለት እፈልጋለሁ ብለዋል፡፡

በመቀጠል የሀገራችን አየር ሁኔታና ጠባይ እንደ ኢኮሎጂና ስነ ምሕዳር ሁኔታ ልዩነት እንደሚኖረው ሁሉ የዝናብ አገባብና አወጣጥ እንዲሁም መጠንና ስርጭቱም የሚለያይ በመሆኑ የመሳሪያው መተከል የአከባቢውን የአየር ሁኔታና ጠባይ በማወቅበ ድርቅና በጎርፍ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ ለመቀነስ ብሎም ለመከላከል እና በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ የጎላ ፋይዳ እንዳለው አስረድተዋል፡፡

የደቡብ ክልል የአደጋ መከላከል ቢሮ ኃላፊ አቶ አበራ በበኩላቸው ዓለም በአየር ጠባይ ለውጥ እየተናጠች ባለችበት በአሁኑ ወቅት ተፅዕኖው የሚከፋው እንደኛ ሀገር ኢኮኖሚያቸው በግብርና ላይ መሠረት ያደረገ በተለይም ግብርናቸው ከዝናብ ጥገኝነት ባልተላቀቀባቸው ሀገራት ችግሩ የከፋ መሆኑን ጠቅሰው የዝናብ መጠንና ሥርጭት መዛባት ዜጎችን ለምግብ እጥረት ከመዳረጉም ባሻገር በሀገር ኢኮኖሚ ላይም ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ መሆኑን ጠቅሰው የዝናብ እጥረት በሚጠበቅበት ወቅት መረጃውን አስቀድሞ ማግኘት ከዘር መረጣ ጀምሮ የአፈር እርጥበትን በማቆየት ፈጥነው ሊደርሱ የሚችሉ

ሰብሎችን ለመዝራት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው ገልጠዋል፡፡

አቶ አበራ በመቀጠል አሁን የሚቲዎሮሎጂ መረጃ ለዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚኖረውን ፋይዳ ህብረተሰቡ እየተገነዘበ በመጣበት ወቅት እነዚህ መሣሪያዎች በክልላችን በመተከላቸው የተሰማቸውን ደስታ በመግለፅ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና የአከባቢው ህብረተሰብ የተቋቋሙ መሣሪያዎችን በመንከባከብና ደህንነታቸውን በአግባቡ በመጠበቅ በኩል የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አሳስበዋል፡፡

ለጋሽ ድርጅትን በመወከል ንግግር ያደረጉት የሥራ ኃላፊ አቶ ንጉሴ አክሊሉ ምንም እንኳን መሣሪያዎቹ ከፍተኛ ወጪ የወጣባቸው ቢሆንም ከኤጀንሲው ጋር ተቀናጅተን በመሥራታችን መሣሪያዎቹ ያለምንም ቀረጥ እንዲገቡ በማድረግ ተጨማሪ ወጪን ማስቀረት የተቻለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በሌላ መልኩ በፕሮጀክቱ በኤጀንሲው የሚሰጡ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ወደ እነዚህ አካባቢዎች ማድረስ እንዲቻል ሥራዎች መከናወናቸውን ለአብነት ሲያነሱ የሚዲያ ባለሞያዎችን የማሰልጠን፣ ለሚዲያ ተቋማት ተገቢው ወጪ እንደሚሸፈን ውል የመዋዋል፣ አርሶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ መረጃውን የሚከታተልበት ሬዲዮ በመግዛት ጣቢያው በተቋቋሙባቸው ሦስቱ ክልሎች መሰጠቱን ጠቅሰው በዚሁ መሠረት በየ3 ቀኑና በየ10 ቀኑ በአሥር የአካባቢ ቋንቋዎች የአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃዎችና ቴክኒካዊ ምክሮችን የመስጠት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ገልጠዋል፡፡

በመጨረሻም የተተከለው መሳሪያ በይፋ ከተመረቀ በኋላ የወረዳው አስተዳዳሪ የጣቢያውን አስፈላጊነት በመገንዘብ የመንከባከብ ኃላፊነት የሁሉም ቢሆንም የሀገር ሽማግሌዎችና የአካባቢው ህብረተሰብ በባለቤትነት እንዲረከብና አንዲንከባከብ ባስተላለፉት ጥሪ መሠረት ቃል በመግባት ተረክበዋል፡፡



ዘመናዊ የሚቲዎሮሎጂ መረጃ መሰብሰቢያ ጣቢያ ርክክብ ከኅብረተሰቡ ጋር ሲካሄድ


NOAA
NMA
ብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ
NATIONAL METEOROLOGY AGENCY
USAID
FROM THE AMERICAN PEOPLE
ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ የበጋ ወቅት የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ይፋ
ለማድረግና ባለፈው ክርምት ወቅት የተሰጠውን ትንበያ በተጨባጭ
ከተከሰተው ጋር በማነፃፀር ያለውን ሁኔታ ከደንበኞቹና ባለ ድርሻ አካላት ጋር
ለመገምገም ያዘጋጀ የምክክር መድረክ!!
መስከረም 15/ 2010 ዓ.ም አዲስ አበባ
sayas
Advert And Art Studio
0911-638907























